የረቡዕ ሰኔ 22  1097 ዓም( የጁን 29 2005)

## የፍኖተ ዴሞክራሲ ሐተታ

### የሕዝቡ ትግል ትኩረቱን እንዳያጣ

### አቅጣጫውንም እንዳይስት

ከግንቦት ወር ጀምሮ  የኢትዮጵያ የፖሊቲካ ሁኔታ በማያሻማ መልኩ በመለወጥ ላይ መሆኑ ብዙ ትንታኔና ገለጻ የሚያስፈልገው አይደለም። ከአስራ አራት ዓመታት የአምባገነን አገዛዝ በኋላ፥ ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ በመላው የሀገሪቱ ክፍሎች ሰላማዊ አመፅ በማድረግ ላይ ይገኛል። አመፁን የቀሰቀሰው የወያኔ አሰቃቂ አገዛዝ ውጤት እንጅ ማንም አልነበረም። ከጭቆናውና ከውርደት በመነጨ ብሶት ሕዝቡ እንደማዕበል ገንፍሎ ወጣ እንጅ፥ ማንም ክፍል ሳይፈልግ የለኮሰው፥ ያቀጣጠለውና ያስኬደው አልነበረም። ለወያኔና ለግብረ-አበሮቹ ዱብ-ዕዳ የሆነባቸውም ለዚህ ነው። “ድል አባቷ ብዙ ነው ሽንፈት ግን የእንጀራ አባት እንኳ  አይኖራትም” እንደሚባለው፥ ዛሬ አንዳንድ ክፍሎች የድል አጥቢያ  ሰብዕና  ለማግኘት ቢቃጡም፥ ከግንቦት ወር ጀምሮ በመካሄድ ላይ ያለው ሰላመዊ-ሕዝባዊ አመፅ  ከኢትዮጵያ ሕዝብ ብሶትና እሮሮ ማህፀን የተወለደ ነው። ይህ ሕዝባዊ አመፅ፥ በተለያዩ ምክንያቶች ለጊዜው ጋብ ሊል ይችል እንደሁ እንጅ፥ የማንም አሻጥር፥ የዲፕሎማሲ ሽርጉድ፥ የአንድ አንድ ክፍሎች መውገርገር፥ ወይም የወያኔ ግድያና ጭፍጨፋ እስከናካቴው ሊያቆው አይችልም።  የስድሳ ስድስቱንም ሕዝባዊ አመፅ ለማዳፈን ተሞክሮ ነበር ግን አልተሳካም። ሕዝባዊ ኃይል የመጨረሻ አቸናፊ መሆኑ በታሪክ የተመሰከረ ዕውነታ ነው።

ማነኛውም ኅብረተስብ ከታሪክ መማር ይገባዋል ከተባለ፥ የአለፉት ሠላሳ ዓመታት የሀገራችን የትግል ታሪክና የሦስቱም ተፈራራቂ አምባገነን ሥርዓቶች ብዙ፥ እጅግ ብዙ ትምህርቶችን ሊያስተምሩ ችለዋል። የሀገራችን ሕዝብም ከታሪክ የሚማር ዜጋ በመሆኑ፥ የቀሰመውን ተመክሮ ጊዜው ሲደርስ በተግባር መተርጎሙ የማይቀር ነው። መለስና ጥቂት ተባባሪዎቹ፥ ይህንን ታላቅና ታሪካዊ ሕዝብ፥ ቢንቁትም፥ ቢያዋርዱትም፥ ቢጠሉትም፥ ቢዘርፉትም፥ ቢበድሉትም፥ ቢከዱትና አሳልፈው ቢሰጡትም፥ ሊያለያዩትም ቢጥሩ፥ ክብሩንና ታሪኩን፥ ባኅሉንና መስተጋብሩን፥ ሰብዓዊ መብቱንና የዜግነት ታሪኩንና አንድነቱን ጠብቆ፥ ለነፃነቱና ለዴሞክራሲያዊ መብቱ መታገሉ የማይቀር ነው። ታግሎም ድሉን እንደሚጎናፀፍ ጥርጥር አይኖረንም። ለዚህም ነው እኛ ከሕዝባችን ጎን በመቆም ግንባራችንን ሳናጥፍ፥ ለማንም ሳንበረከክ፥ ብኩርናችን በጊዚያዊ ጥቅም ሳንለውጥና በሀገራችን ብሔራዊ ጥቅም ላይ ሳንደራደር፥  በአቋማችን ፀንተን የኢትዮጵያን ሕዝብ ውሳኔ የምናከብረው። በአሁኑ ወቅት፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ውሳኔ ምንድን ነው?

ብለን ስንጠይቅ፥ እምቢኝ ለአምባገነን ሥርዓት ብሎ መታገል የሚል መልስ እናገኛለን:: መልሱ ታዲያ ይህ ከሆነ፥ ከሕዝቡ ጋር ወገንተኝነታችንን ከመግለጽ በቀር ለሌላ አማራጭ ሊኖረን አይችልም:: ከዚህ ውጭ ሌላ መንገድ ለመፈለግም ታሪካችን አይፈቅድልንም:: በማያጠራጥር መልኩ ከሕዝባችን-ከወገናችን ጎን ቆመን እንታገላለን::

የሕዝባችን ውሳኔ፥ ለዴሞክራሲ መብቶች አምርሮ መታገል ከሆነ፥ ይህ ትግል አቅጣጫውን እንዳይስት፥ ትኩረቱን እንዳያጣና በወያኔ አሻጥርና ማስፈራራት እንዳይከሸፍ፥ ብርቱ ጥንቃቄ መደረግ ይኖርባታል:: በአሁን ሰዓት መለስና ጥቂት ግብረ አበሮቹ፥ እንደ ቆሰለ አውሬ ተቅበዝብዘዋል:: እንደ ተተኮሰበት ድኩላም ግራ ተጋብቷቸዋል:: ይህ ማለት ግን የሚሰሩትን አያውቁም ማለት አይደለም:: ትኩረትም የላቸውም ማለት አይደለም:: በዕርግጥ የሚሰሩትን ያውቁታል:: በቅርብ ዕርቀት ያነጣጠረ ትኩረትም አላቸው:: ወቅታዊ አጀንዳቸውም አሁን ከገቡበት የፖሊቲካ ማጥ የፈለገውን ሁሉ ፈፅመውና ሰርተው መውጣት ነው:: ይህንም ለማድረግ ደግሞ ቅድሚያ የሚሰጡት የሕዝቡን የትግል አቅጣጫ ለማስለወጥ መሞከር ይሆናል:: ወደተግባር ለመለወጥ ከሚያስችሏቸው ዘዴዎች መካከል ዋነኛው፥ የትግራይን ሕዝብ፥ ከቀሪው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ለማቃቃር የሚያደርጉት እኩይ ተግባር እንደሆነ ዛሬ ሁሉም ነቅቶባቸዋል:: በተለይም አንድ አንድ ኅሌናቸውን የሸጡና ከአንድ ምዕራፍ የበለጠ ርቀት ለማየት ያልታደሉ ምሁራንን ለዚህ ዘዴያቸው ይጠቀሙባቸዋል:: ሰሞኑን በየስብሰባውና በየኤሊክትሮኒክስ መገናኛ ብዙኀኑ የሚያስራጩት መርዘኛና አደገኛ ጽሁፎች በቂ ማስረጃ ሆነዋል:: ይህ፥ ሕዝብን ከሕዝብ የሚያፋጅና የሚያለያይ መርዘኛ ፕሮፓጋንዳ፥ በዘለቄታ መልኩ የሚያመጣው ሰበብ ብርቱ ነው ለማለት ባይቻልም፥ ምናልባት ወያኔን አሁን ከገባበት ማጥ ለመውጣት በሚያደርገው መፍጨርጨር፥ ጊዘያዊ የሆነ የዕፎይታ ጊዜ ሊያስገኝለት ግን ይችል ይሆናል:: ይህ ሊሆን የሚችለው ግን፥ የፖሊቲካ ድርጅቶችና መላው ኅብረተሰብ የወያኔ ተንኮለኛ ፕርፓጋንዳ ሰለባ ሲሆኑ ብቻ ነው:: አቅጣጫ ለማስቀየር ሲል ከሚጠቀምባቸው ተንኮሎች ውስጥ፥ ጭራሮ የሆኑ አስቂኝ ሁኔታዎችን በመፍጠር ሕዝቡ ስሜታዊ በሆኑ ነገሮች ላይ እንዲያተኩር ማድረግ ነው:: የኦሮሞ ድርጅቶችን ጊዜያዊ ድጋፍ አገኝበታለሁ ብሎ በመገመት፥ የኦሮሞ ዋና ከተማ ፍንፍኔ ነው ብሎ አውጇል:: ትላንት አዳማ ነው መሆን ያለበት ብሎ እንዳልወሰነ ሁሉ ማለት ነው:: ይህ ተልካሻ ዘዴ፥ የኢትዮጵያን ሕዝብ ሥነ አዕምሮ ካለመረዳት የመጣ ድፍረት ብቻ ሳይሆን፤ የወያኔ መሪዎች አስተሳሰብ ከአፍንጫቸው የማይርቅ መሆኑን በድጋሚ አረጋግጧል:: ምንም ምን ርካሽና ተራ ማጭበርበር ቢጠቀምም፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን ነቅቶበታልና ከመጤፍ አይቆጥረውም:: "ጅብ የሚያነከሰው ሜዳ እስኪያገኝ ድረስ ነው" እንደሚባለው፥ መለስ አሁን ዙሪያው ገደል የሆነበት መስሎ ለመታየት ቢሞክርም፤ ነገ፥ ጊዜ አግኝቶ ከተንሰራራ፥ ቂሙን ረስቶ ሁሉንም ነገር በአርምሞ ይመለከታል ማለት ዘበት ነው:: እነመለስ፥ እንደ ድርጅትም ብቻ ሳይሆን፥ በግለሰብ ደረጃ ቂምን አርግዘው፥ በቀልን የሚወልዱ ግለሰቦች በመሆናቸው፥ ወሰን የሌለው የኃይል ርምጃ በመውሰድ ተቃዋሚ ነው

የሚሉትን ሁሉ ለማጥፋት ወደኋላ እንደማይሉ መታወቅ አለበት:: አሁንም የሚያደርጉት የሠላማዊ ሕዝብ ጭፍጨፋ፤ አፈናና ዕስራት ከዚህ መሠረታዊ ባኅርያቸው የመነጨ ነው::

ይህን ሁኔታ በሚገባ መረዳት ከቻልን፥ በአሁኑ ጊዜ ምን መደረግ ይኖርበታል? በዕኛ ዕምነት፥የሕዝቡና የተቃዋሚው ጎራ በመተባባር የሚከተሉትን ጉዳዮች በቅደም ተራ መፈፀም አለባቸው እንላለን::

- ሕዝቡና ተቀዋሚው የማይናወጥ መሠረታዊ ግንኙነትና ትብብር መፍጠር አለባቸው::

- በዘር፥ በኃይማኖትና በፖሊቲካ ምክንያት ልዩነት ተፈጥሮ፥ ፍጅት እንዲመጣ የሚደረገውን የወያኔን ተንኮል ነቅቶ በመጠባበቅ ማክሸፍ ያስፈልጋል::

- ልዩ ልዩ የትግራይ ቡድኖችና ምሁራን የወያኔን ከፋፋይ ተንኮል በማክሸፍ ረገድ ወሳኝ ሚና እንደሚጫወቱና ከባድም ኃላፊን እንዳለባቸው መረዳት፥ ከቀሪው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ኀብረታቸን አጠንክረው ወያኔን መዋጋት፥ የዴሞክራሲ ሥርዓት እንዲመጣ በሚደረገው ትግል የድርሻቸውን መወጣት፥

- ምን ጊዜም ቢሆን ማነኛውም ባዕድ ለኢትዮጵያ መልካም ሊያስብ ይችላል ብሎ በመታለል የራስን ግዴታ ከመወጣት አለመዘናጋት፥

- የኃይማኖት ተቋማትና አባቶች፥ ሼኮች የወቅቱን የሀገራቸውን ሁኔታ በአርምሞ እንዳይመለከቱት፥ ይልቁንም ሀገርን ነፃ ለማውጣት በሚደረገው ትግል የሚያበረክቱት ድርሻ ታሪካዊ እንደሆነ መረዳት:: ተሳትፏቸውን ማስተባበር፥ ማመቻቸት፥

- የሴቶችና የወጣቶች የትግል ድርሻ ወሳኝ መሆኑን ተገንዝቦ፥ ሰፊና ንቁ ተሳትፎ የሚያደርጉበትን ሁኔታና መድረክ ማዘጋጀት፥

- ለማነኛውም እንቀስቃሴ የገንዘብ ኃይል እጅግ ወሳኝ መሆኑን ተረድቶ፥ ባለሀብቱና ሁሉም ባለአቅም ዜጋ እጁን መዘርጋት

- በውስጥና በውጭ የሚገኙትን የኢትዮጵያ ምሁራን ዕውቀትና ተመክሮ፥ ሙያና ችሎታ ለማስተባበር መጣር፤ የኢትዮጵያ ትግል፥ ታጋይ ድርጅቶችን ብቻ ሳይሆን፥ስትራቴጂያዊ ራዕይን የሚነድፉ ሊቃውንት የሚያስፈልጉት መሆኑን መዘንጋት ስለሌለበት የኢትዮጵያን ምሁራን ማሳተፍ እጅግ ወሳኝ መሆኑ መታወቅ ይኖርበታል::

- ምንም እንኳ በዘለቄታ መልኩ፥ የኢትዮጵያን ዕድል የሚወስነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ብቻ መሆኑ ባይዘነጋም፥ የዓለም አቀፍ ርዳታና ዲፕሎማሲ የሚያበረክተው ድርሻ በቀላሉ ስለማይገመት፥ ይህንኑ ጉዳይ በተቀነባባረና ቀጣይ በሆነ መንገድ ማንቀሳቀስ አስፈላጊ እንደሆነ መረዳት ያስፈልጋል።

እንግዲህ ከሞላ ጎደል ከላይ የተዘረዘሩትን ሁሉ በቅደም ተከተል አስገብቶ፥ መታገል ከተቻለ፤ ወያኔና ጥቂት ግብረ-አበሮቹ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የማይንበረከኩበት አንዳችም ምክንያት አይኖርም። ዋናው ጉዳይ ትግልን ማፋፋም ነው። ከወያኔ ደግና በጎ ነገር የሚጠበቅ አይደለምና የፈሰሰው የዜጋ ደም መና እንዳይቀር ወንጀለኛውን አገዛዝ በአመረረ ትግል ከታሪክ ትቢያ እንጣለው። ጠላታችን እንዲያንሰራራ፤እየከፈፋለ እንዲመታን ጊዜ አንስጠው።